https://www.path-2-happiness.com/am

## ነቢያዊ ሱንና ውስጥ፦

ወደ ነቢያዊ ሐዲሶች ዐጸድ ከሄድን፣በምስጉን ስነምግባራትና በትሩፋት መርሆዎች የጎመሩ፣ልንቀጥፋቸው የምንችል ብዙ የኢማን ዛፎችን እናገኛለን። ከነዚህ ውስጥ፦

- ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ገር፣ለስላሳ፣የማያካብድና ለሰዎች ቅርብ የሆነ ሰው ሁሉ በእሳት ላይ እርም ተደርጓል።›› [በትርምዚ የተዘገበ]
- የአላህ መልክተኛ ﷺ ለአንድ ሶሓቢይ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹አላህ የሚወዳቸው ሁለት ባሕርያት አሉህ፦ ቻይነት (ታጋሽነት) እና ረጋ ባይነት።›› [በአሕመድ የተዘገበ]
- በተጨማሪም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹እኔ ዘንድ ያለውን ነገር ከናንተ ቆጥቤ አላስቀምጥም፤ራሱን ቁጥብ ማድረግ የፈለገን ሰው አላህ ቁጥብ ያደርገዋል፤ራሱን ማብቃቃት የፈለገን ሰውም አላህ የተብቃቃ ያደርገዋል፤ራሱን ማጽናናት የፈለገን ሰውም አላህ ያጽናነዋል፤ለማንም ሰው ከትእግስት የበለጠ መልካምና ሰፊ ስጦታ አልተሰጠም።›› [በሙስሊም የተዘገበ]
- በተጨማሪም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ሀብታምነት በንብረት ብዛት ሳይሆን፣ሀብታምነት የመንፈስ ሀብታምነት ነው።›› [በቡኻሪ የተዘገበ]
- የአላህ መልክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ሰዎችን የማያመሰግን አላህን አያመሰግንም።›› [በአሕመድ የተዘገበ]
- በተጨማሪም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ራሳችሁን አስተናንሱ (ትሁት ሁኑ)፤አንዳችሁ በሌላኛው ላይ ወሰን አይለፍ የሚል ከአላህ ተላልፎልኛል።›› [በእብን ማጃህ የተዘገበ]
- በተጨማሪም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ሁሉም መልካም ሥራ ሶደቃ ነው፤ከመልካም ሥራ ውስጥ አንዱ፣ወንድምህን በፈካ ፊት መቀበል ነው፤ከራስህ ባልዲ ወደ ወንድምህ ዕቃ ውሃ መገልበጥም ነው።›› [በትርምዚ የተዘገበ]

በመጨረሻም በእውነተኛው ደስተኝነትና በመልካም ስነምግባራት መካከል ያለውን ግንኙነት፣በጣም ጥብቅ ጽኑና የተሳሰረ ጠንካራ ግንኙነት ሆኖ እናገኛለን። ግብረ ገብነትና መልካም ጠባይ ለሰው ልጆች ደስተኝነትና መታደል ብቸኛው ምንጭ ነው። ያለ ምስጉን ስነምግባር ደስተኝነት ፈጽሞ የሚታሰብ አይደለም። መልካም ስነምግባር በሌለበት ሁኔታ የሰው ልጅ በሕይወቱ ውስጥ ተስፋ መቁረጥን፣ጭንቀትን፣አበሳባና መከራን፣ውጥረትና መብሰልሰልን ብቻ ነው የሚያመርተውና የሚሰበስበው። በመሆኑም ደስተኝነትና መታደልን ፍለጋ፣የሰው ልጅ መልካም ስነምግባራትን እንዲላበስ ከሚገፋፉ አበይት ጉዳዮች ዋነኛው ነው። ምክንያቱም ያለ ምስጉን ስነምግባር ለአንዲት ሰከንድ እውነተኛውን ደስተኝነትንም ሆነ አንድም ቀን እርካታና መታደልን መጎናጸፍ እንደማይችል በእርግጠኝነት ያውቃልና።



https://www.path-2-happiness.com/am